# እስቲ እንቀኝ ...

*እንብላ ካላችሁ፣ እንጠጣ ካላችሁ፣*

*ምግብ እንምረጣ ...?*

*አሰሱን ገሰሱን ክኩን ወዲያ በሉ፣*

*ክተፉ ምተሩ - ጣፋጭ ዱለት ሥሩ!!*

*ምን ያደርግልኛል ጥሬው የሥጋ አይነት*

*ምናምኑ ጣፊያ፣*

*ዱለት ነው ያማረኝ*

*እንዴት ዱለት ጠፋ?!!*

<u>ማብራሪያ፡-</u> በቀደም ዕለት ወደ ዋሽንግተን ዲሲ ብቅ ብዬ የኢሕአፓን 39ኛ የምሥረታ በዓል ለመሳተፍ እድል አግኝቼ ነበር። በበኩሌ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ኢሕአፓንና ታሪካዊ ሂደቱን ሳላወሳ የሚያልፉኝ ቀኖች ላለማጋነን ያህል ጥቂቶች ቢሆኑም፣ በክብረ በዓሉ ላይ ለመገኘት ያስወሰነኝ ዋናው ጉዳይ ከሌላ አንጻር ኢሕአፓን ለማየት ነበር - የሚያከብሩትንና ትዝታው የሚናፍቃቸውን ወገኖችን በአንድ ላይ ለማግኘትና ስሜታቸውን ለመጋራት። አደራሹ ሞልቱ፤ ምግብና መጠጡ ተደርድሮ ሁሉም ትዝታውንና አኩሪ ታሪኩን እየተቀባበል ሲሟሟቅ ውልብ ብሎብኝ አንገቴን ደፍቸ ከላይ ያሰፈርኳቸውን መስመሮችና ዘግየት ብላችሁ የምታዩትን ስንኝ ጫር ጫር አደረኩ።

ባህላዊው የቅኔ ወጋችን ውስጣዊ መልእክቱ የተወሰነ ጊዜንና ሁኔታን የጨበጠ ነው። ክፉም ይሁን ደግ፣ ደስታም ይሁን ምሬት .... ቅኔው በወረደበት ወቅት ላይ የሚንጸባረቅ ነው። በሌላ በኩልም አንድን የቅኔ መልዕክት የተለያዩ ሰዎች ከገጠመኞቻቸውና ከሚረዱት ሁኔታ ጋር አገናዝበው በተለያየ መልክ ሊተረጉሙት የመቻላቸው አቅም አይዘነጋም። እንዲህም ሆነና በኢሕአፓ 39ኛ ክብረ በዓል ላይ ሁሉም ተደስቶ ሲበላ ሲጠጣ ሕዝባችንና ሀገራችን ያሉበት ተጨባጭ ሁኔታ ትዝ ብሎኝ ያን ለመግለጽ የሞከርኩበት ነው።

የመጀመሪያው ግጥም ልባስ (ሰም) መብላትና መጠጣት ከፈለጋችሁ ያረባባውን ነገር ትተን ከተፍ ከተፍ አርገን ጥሩውን የምግብ አይነት ዱለት ሠርተን እንበላ እንደማለት ሲሆን፤ የመለእክቱ ደም-ሥር (ወርቁ) ግን ያሰባችሁት እንዲሳካ ከፈለጋችሁ፣ በጠላታችሁ ላይ ቀርጣችሁ አሲሩ፤ አድሙ እንደማለት ነው።

ሁለተኛው የግጥም ምት ከመጀመሪያው የቀጠለ ነው። አላባሽ መለእክቱ (ሰሙ) ያልበሰል የሥጋ አይነት፣ እንደ ጣፊያ የመሳሰለውን አልፈልግም፤ ለመብላት ያማረኝ ዱለት ነውና ምነው ዱለት ሥጋ ጠፋ የሚል ሲሆን፣ የግጥሙ ልብ(ወርቁ) ግን ያረባባ ነገር ወንዝ አያሻግርምና ማሴር (ማደም) ነውና የሚያስፈልገው እንዴት ማሴር አቃተን፣ እንዴት ማደም ከበደን የሚል የምሬት ቃል ነው።

……///////……………

*ያገን የታሪክ በር …*

*ውሽልሽል ነው ሲሉ - ሰው የለውም ጎራው፣*

*ጥሰን ደረማምሰን እናልፋለን ሲሉ፣*

*እዩት ብረት ሆነ - እንዲህ ተባ በሩ!!!*

ከዚህ በላይ የሰፈረችው መልዕክት በዚያው ዕለት በኢሕአፓ 39ኛ ክብረ በዓል ላይ ከአፍ እስከ ገደፍ አደራሹ ሞልቶ ቤቱ በደስታ ተሞልቶ ስመለከት ለዚያ መልእክት ትሁንልኝ ብዬ የጫርኳት ናት።

በቀላል መልእክት ደረጃ (ሰሙ) በሩ ሰው ያልቆመበት ከዚህ ግባ የማይባል ጎራ ነው ብሎ በማሰብ በቀላሉ ደረማምሰን እናልፋለን ሲሉ ጠንካራ ሆኖ አገኙት እንደማለት ሲሆን፤ አይነታው መለእክት (ወርቁ) ግን የሚገኟቸውን ጠላቶቻቸውን እንዲህ በመተባበር አሳፍረዋል፣ በአደራሹ ሞልተው ተባብረው ቆመዋል፤ በጠላቶቻቸው ላይ እንድነታቸውን አጠናክረዋል .. እንደማለት ነው።

እስቲ ሁላችንም ይህ የሥነ-ጽሁፍ ባህላችንና የዕውቀት መሥፍርታችን እንዳይደበዝዝ በያለንበት የኔ ብለን በመያዝ እናዳብረው፤ ልዩ የሆነ የሃሳብ ማዳወሪያ መሳሪያችን ከመሆኑ ሌላ አባቶቻችንና እናቶቻችን ለዘመናት የተጠቀሙበት ሚስጥራዊ መለእክት ማስተላለፊያ ቅርስ ነውና ችላ ልንለው ከቶ አይገባም።

ከምስጋናጋ፣

(ሙሉቀን)